# ክብሩንና ሕይወቱን ለልጆቹ  ሰዋ !

ከበልጅግ አሊ

-፩-

አንዷት አይጥ ከአንዱ ሥፍራ ወደ ሌላው ሥፍራ ትራወጣለች ። ሰውየው አይጧን ይይዝና ምን ሆነሽ ነው እንዲህ የምትሮጪው ይላታል ። አይጧም አልሰማህም እንዴ ! ? በሃገር ውስጥ የሚገኙ  ዝሆኖች በሙሉ ይገደሉ ተብሏል እኮ አለችው ። ሰውየው ታዲያ አንቺ ዝሆን አይደለሽ ምን አስፈራሽ ? ብሎ ይጠይቃታል ። አይጧም እስኪጣራ  ብለው ቢይዙኝስ አለች ይባላል ።

ይህንን ቀልድ በደርግ ዘመን የሰማሁትም ቢሆን እንደገና አሁን  ሳስታውሰው ያስደስተኛል ።በደርግ ዘመን በአይጥና በዝሆን መካከል ዓይነት ያለው ልዩነት እስከሚጣራ ብዙ ሰዎች ታስረዋል ተገድለዋል ። „የደርግ አገር ወዳድነት“ ፣“ የመንግስቱም ቆራጥነት“ በእርግጥ እስከሚታወቅ  አስራ ሰባት አመት ያህል ወስዷል ።  ከዚያም በኋላ ያስከተለው ጉዳት ሁላችንም አይተን ታዝበን ያለፍንበት ሆኖ ሳለ <<ደርግ አገር ወዳድ>> ነው ፣ <<መንግስቱም ቆራጥ ነበሩ>> ብለው የሚፅፉ ፣ በየፓልቶኩ  የሚዘባርቁ የኢሠፓ ካድሬዎች አሁንም አልጠፉም ።

በቅርብ ጊዜ ሁለት የደርግ - ኢሠፓ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ሁለት መፀሐፍት ለንባብ አብቅተዋል ። ዘነበ ፈለቀ የኢሠፓ ከፍተኛ ባለሥልጣንና የደርግ ውስጥ አዋቂ <<ነበር ቁጥር ሁለትን>>  ሲፅፍ ፣ የደርግ የስለላ መዋቅር አባል የነበረው ተስፋዬ ርስቴ ደግሞ <<ምስክርነት በባለሥልጣኑ አንደበት>> የሚል መፀሐፍ ለንባብ አብቅቷል ። <<ነበር ቁጥር ሁለት>> <<ከነበር ቁጥር አንድ>> በጣም በተሻለ ሁኔታ የተፃፈ ሲሆን <<ምስክርነት በባለሥልጣኑ አንደበት>> ግን የአሉ አሉና በጥድፊያ የተፃፈ ሆኖ አግኝቼዋልሁ ። በተለይ በወያኔ እስር ቤት ውስጥ ያሉት እስረኞች ተስፋዬ ዕርስቴን በወያኔ ሰላይነት ሰለሚጠረጥሩት ለፀሐፊው የሰጡት ቃለ መጠይቅ እውነተኝነቱን ጥርጣሬ ውስጥ ይከታል ። በመፀሐፉ ገፅ ( መግቢያ ገፅ XI ) ላይ እንዲህ ይላል ፤

<< አንድ ከፍተኛ የኢሕድሪ ባለሥልጣን እስረኛ ባለሥልጣናት እንዳይተባበሩ << እኛን እየጠየቀ መረጃ ለወያኔ ያቀብላል >> በማለት የሐሰት ወንጅለውት ነበር - ፀሐፊውን ። ወዲያውኑ ሰንዳፋ ፖሊስ ኮሌጅ ታስረው ነበሩ የቀድሞ ባለሥልጣናት ወደ ማዕከላዊ እስር ቤት ተዛውረው ሲመጡ << ለወያኔ መረጃ ያቀብላል >> የሚለው ስም <<ለአንድ የኢሠፓ ከፍተኛ ባለሥልጣን ኢኮኖሚስት ደረሰና ወሬው እንደ ሰደድ እሳት ለሁሉም አዳረሱት ። ፀሐፊውን ሁሉም ሰው ፈራው ።>>

ከዚህ አባባሉና በተለይ ፀሐፊው በመፀሐፉ ውስጥ ወያኔን ላለማጋለጥ ያደረገውን ጥረት ልብ ብዬ ስመረምረው ፀሐፊው ለወያኔ ነው የሚሰራው የሚለውን ጥርጣሬዬን ያጎላዋል ። በተለይ በተለያዩ ስለ ደርግ መንግሥት የተፃፉት መፀሐፍት ውስጥ እንደተጠቀሰው የደርግ የስለላ መዋቅር ውስጥ ከሚሰሩት ሰራተኞች ውስጥ አንዳንዶቹ (አለቃቸውን ተስፋዬ ወልደስላሴን ጨምሮ )  ለወያኔ ይሠሩ ነበር የሚለውን ሃቅ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል ። <<ምስክርነት ባለ ሥልጣኑ አንደበት>> የሚለው መፀሐፍ ላይ ወደ ፊት በሌላ ፅሁፍ በሰፊው እመለስበታለሁ ።ለዛሬው ግን <<ነበር ቁጥር ሁለት>> ላይ የተፃፈ አሳዛኝ ታሪክ ላይ ላተኩር ።

<<ነበር ቁጥር ሁለትንና>> <<ምስክርነት በባለሥልጣናቱ አንደበት>> የሚሉትን መፃሕፍት ለመዋስ ወደ ከተማ ብቅ ባልኩበት ቀን  መጻሕፍቱን ያመጣልኝ ግለሰብ ጋር ባቡር ጣቢያ ቆንመን  ባቡር ስንጠብቅ እንደ ድንገት - <<ጄነራል ዘለቀ በየነ ማለት ይሄ ነው ። መጻሕፍቱ ውስጥ ሰለ እሱ ብዙ ታነባለህ። ይህ ፋሽስት በጀርመን ዜጎች  ቀረጥ ከፋይነት ትከሻ  እዚህ ተንደላቆ ይኖራል>> ብሎ  አንድ መካከለኛ ቁመት ያለው ሰው አሳየኝ።

<<ነበር ቁጥር ሁለትን>> ሳነብ ሰለ ጄነራል ዘለቀ በየነ  የተፃፈው ዓለም ምን ያህል በመድሎ የተሞላች ነች ብዬ እንዳስብ አድርጎኛል ። የብዙ ንፁሃን ደም በእጁ ያለበት በየነ ዘለቀ በአውሮፓ ውስጥ በነፃነት ይንደላቀቃል ። በዚህ ፋሽስት የተገደሉ ፣

አካላቸው የጎደለ ፣ ለልጆቻቸው ሲሉ ሕይወታቸውን ያጠፉ ፣ የተደፈሩ ልጃገረዶች ፣ ልጆቻቸውን ያጡ እናትና አባቶች ፣ ባሎቻቸውን ያጡ ወጣት ሴቶች ፍትሕን ሳያገኙ በዛች ሃገር እየተሰቃዩ ዘለቀ በየነ ግን አሁንም በተንደላቀቀ ኑሮ ያላግጥባቸዋል ።

<<ነበር ቁጥር ሁለት>> የዘለቀ በየነን አሳፋሪ ምግባር የሆነ ታሪክ ይዞ ነው የወጣው ታሪኩን ከመፅሐፉ ላይ እንዳለ አቀርበዋለሁ። ( ገፅ 334 - 336)

# የሜጀር ጀኔራል ዘለቀ በየነ ቅሌት

መሐል ሜዳ (መንዝ ውስጥ) ይዋጋ የነበረ ሠራዊት ተንዶ ሲያፈገፍግ ሜ\ ጀኔራል ዘለቀ በየነ በሄሊኮፕተር አምልጠው ደብረ ብርሃን ገቡ ። ውጊያው ጣርማ በር ላይ ተገታ ። እሳቸው ግን የቀጠና 5 አብዮታዊ ዘመቻ አስተባባሪ ተብለው ወደ ደቡብ ምዕራብ ተዛወሩ ።

ወደዚያ እንዲዛወሩ የተደረገው ከደቡብ ወሎ ውድቀት በኋላ በቀጠና 3 አብዮታዊ ዕዝ ሥር ከእርሳቸው ጋር አራት ሜ\ ጀኔራሎች በመጠራቀማቸው ተራፊውን ሠራዊት ለእነዚህ ጄኔራሎች ዕዝ ሰለሚያንስ ብዛታቸውን ለመቀነስ ቢመስልም በዚህ ብቻ ማጠቃለልም ያስቸግራል ።

የኦነግ እንቅስቃሴ እየሰፋና ውጊያውም እየበረታ በመሄዱ በደቡብ ምዕራብ አካባቢ በርካታ ክፍለ ጦሮች ተከማችተዋል ። ኢሕአዴግም ባህር ዳርን ከያዘ በኋላ በቡሬ በኩል ወደ ወለጋ መሻገሩ እንደማይቀር ታምኗል። ከሁሉም በላይ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ (ፕሬዘዳንቱ) ማዘዣ ማዕከላቸውን ወደ ደቡብ አዛውረው ውጊያውን ለመቀጠል ያለቸውን ዕቅድ በብዙዎቹ ጄኔራሎቻችው ወደ ጎን ቢገፋም << የፈለገ ይከተለኝ >> በሚል ቁርጥ ሐሳብ እቅዱን ለብቻቸው ለማራመድ ወስነዋል።

እንግዲህ በአንድ በኩል አካባቢውን ከኦነግ የሚያፀዳና የኢሕአደግ እንቅስቃሴ ቢቻል ቡሬ ላይ የሚገታ ፣ ይህም ካልሆነም ወደ ደቡብ አቅጣጫ ( ኢሊባቡር ፣ ከፋና ጎሞጎፋ ) እንዳያመራ መቋቋም ፣ ለተለዋጩ ማዘዣ ማዕከል አመቺ መደላደል መፍጠርና ይህንን ሁሉ የተበተነ ተግባር አሰባስቦ መምራት የሚቻለው ታማኝ ጄኔራል አስፈለገ።

ፕሬዝደንት መንግስቱ እንደማንኛውም አፍሪካዊ መሪ በበላይ አመራር ላይ አመዛኙ ትኩረታቸው ለጥራት ሳይሆን ለሥልጣናቸው ታማኝ ለሆነ ሰው በመሆኑ ሜ\ ጀኔራል ዘለቀ በየነን ከማዕከላዊ ዕዝ አዛውረው በቀጠና 5 አብዮታዊ ዘመቻ ማስተባበሪያ ላይ የነበረውን ክፍተት ተሞላ።

ሜ\ ጀኔራል ዘለቀ እዚያ እንደደረሱ ቅብጥብጥና ነጭናጫ ሆኑ ። አንድም የአመራር ድክመታቸውን ለመሸፈን ፣ አንድም ጨርሶ ተስፋ ከመቁረጥ የተነሳ ይመስላል። ወይም ሰሜን ሸዋ ላይ በኢሕአዴግ ተዋጊዎች ከመከበብ ለጥቂት ያመለጡበትን አጋጣሚ የተሳሳተ ግምት ሰጥተውት ( እንደ ጀብድ ) ቆጥረውት ሳይሆን አይቀርም። መታበይን እብሪት ተጠናወታቸውን ፣ የበታቾቻቸውን ናቁ።

እርሳቸው በደርግ አባልነታቸው የደርግ ተጠሪ እየሆኑ በልዩ ልዩ ሃላፊነት በሠፈሩበት ሥፍራ ሁሉ ከአከናወኗቸው በጎ ተግባራት ይልቅ በሕብረተሰቡ ጎልተው የሚነገሩላቸው << በዋል ፈሰስ >> ድርጊቶቻቸው ናቸው ። ይሁን እንጂ ትጉህ የሥራ ሰው መስለው ለመታየትና ለፕሬዘደንቱ ፍፁም ታማኝ መሆናቸውን ለማመልከት በሚያከናውኗቸው የታይታ ተግባራት ደካማ ድርጊቶቻቸው እየከለሉ ኖረው እስከ ሠራዊት አዛዥነት ደረሱ። ሆኖም ይኸው የተለመደ << በዋል ፈሰስነታቸው >> እስከ ማዘዣ ጣቢያ ተከትሏቸው ሄዶ ስለቀጣዩ ውጊያ ለማሰብና ስልት ለማውጠንጠን በቂ ጊዜ እንዳልነበራቸው አጠገባቸው የነበሩ መኮንኖች በትዝብትም ፣ በንቀትም ፣ በሽሙጥም ያወሩባቸው ነበር ።

አንፃራዊ ሠላምና ፋታ ወደሚገኝበት ቀጠና 5 ከተዛወሩ በኋላ የተለመደው<<በዋል ፈሰስ >> ባሕሪያቸው ከእብሪት ጋር ተዳምሮ ሥልጣነቸውን ከወሰኑ አሳለፈባቸው። በዚህም

የተነሳ የወሊጋ አስተዳደር ፓሊስ አዛዥ የነበረውን ኮሎኔል ደበበ እሸቱን << ስራህን በቅጡ አልከወንክም >> በሚል ሰበብ በአደባባይ በ|ጥፊ መቱት ።

ኮሎኔል ደበበ እሸቱ በምግባሩ ጨዋ ፣ በሥራው ታታሪ ፣ በባሕሪው የረጋና ትሁት እንደነበር የሥራ ባልደረቦቹ ይናገራሉ ። በአደባባይ በደረሰበት ውርደት ምክንያት በታጠቀው ሽጉጥ ወዲያውኑ ግንባራቸውን አፍልሶ ይበቀላቸዋል ተብሎ ሲጠበቅ በዝምታ ወደ ማረፊያ ቤት ሄደና ራሱን ገደለ ። << ልጆቼ የጡረታ መብት (ማሳደጊያ) እንዳላሳጣ ብዬ ጠላቴን መግደል ሲገባኝ ራሴን ገድያለሁ >> የሚል ፅሁፍ የያዘ ወረቀት አስከሬኑ አጠገብ ተገኘ። ለልጆቹ ብሎ ክብሩን ሕይወቱን ሰዋ። በእርሱ አሟሟት ያላዘነ ፣ በጀኔራሉ እብሪት ያልተናደደ አልነበረም።

የነበር ፀሐፊ ዘነበ ፈለቀ ይህንን ሃቅ በመፃፉ ባመሰግነውም ሊገልፃቸው ያልደፈራቸው ብዙ የፋሽሽቶች ተግባራት እንዳሉ እሙን ነው ።ዘነበ ፈለቀ ምን አልባት የዘለቀ በየነ ግፍ እውነቱን ልፃፍ ቢል አንድ መፅሐፍ ላይበቃው ይችላል ።በተለይ በሐረርና በጎጃም ክፍለ ሃገር በዚህ ግፈኛ የተጨፈጨፉ ቤት ይቁጠራቸው እንጂ ተቆጥረው የሚያልቁ አደሉም። ግን እውነት ተደብቃ አትቀርም። በተለይ በደርግ የስለላ መዋቅር ውስጥ የነበሩት እውነቱን ያውቁታልና የተሰራውን ግፍ ሊፅፉት ይገባል ። ብዙዎቹ ግን ይህን እውነት ከመፃፍ በየካቲት 66 የፖለቲካ ትምህርት ቤት የተሰጣቸውን የደርግ ፕሮፖጋንዳ እንደ እውነት ሲፅፉ ስመለከት ለእነዚህ ደርግ ናፋቂዎች አዝንላቸዋለሁ ። የደንቆሮ ለቅሶ - - - - ከሚለው ተረት የማያልፍ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

የጀርመን ሕዝብ ይህንን ፋሽስት ከዚህ በላይ ሊንከባከበው አይገባም ። ምንም እንኳ ሃገራችን ውስጥ ከደርግ የማይሻል ሌላ ዘረኛ የወያኔ መንግስት ቢኖርና ለፍርድ ቢያስቸግርም ( አሁን እንደምንመለከተው ወያኔ እነዚህ የደርግ ፋሽስቶች እየተጠቀመባቸው ስለሆነ ) ዘለቀ በየነ ግን ላጠፋው የንፁኀን ደም በአለም አቀፍ የወንጀለኛ ፍርድ ቤት ቀርቧ ቅጣቱን ሊቀበል ይገባል ። ለዚህም እያንዳንዱ በጀርመን የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል ። ይህ ተግባር በጀርመን የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሃላፊነት ብቻ ሳይሆን በዓለም ዙሪያ ያሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በየአካባቢያቸው በደርግ ጊዜ ሲያስሩ ፣ ሲገርፉ ፣ሲገሉ የነበሩትን ለፍርድ ለማቅረብ በአንድ ድምፅ መነሳት ያስፈልጋል ።

እንደ ዘለቀ በየነ ዓይነት ፋሽስቶች በአሁኑ ወቅት በአለም ዙሪያ ተበትነው ይገኛሉ ። ወያኔ ደግሞ ተቃዋሚዎችን በደርግ ደጋፊነት ይወነጅላል ። ያ እንዳይሆን ከተፈለገ ተቃዋሚዎች በግልፅ የደርግን ፋሽሽታዊ መንግስት ማውገዝ ይኖርባቸዋል ። ተቃዋሚዎች የሚታገሉት ደርግን ለመመለስ ሳይሆን ዴሞክራሲን ሀገራችን ውስጥ ለማምጣት መሆኑን ድምፃቸውን ጎላ አድርገው ከደርግ ኢሠፓ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌላቸው ማሳወቅ ይኖርባቸዋል ። በተለይ እንደነ ዘለቀ በየነ ዓይነቶችን በስብሰባቸውም ላይ ቢሆን ማስተናገድ አይኖርባቸውም ።

ለሃገራቸውና ለልጆቻቸው ሲል ራሳቸውን የሰዉ እንደ ኮሎኔል ደበበ እሸቱን ታሪክ ሁል ጊዜ ያስታውሳቸዋል ። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በማይፋቅ ቀለም ተፅፈው ለዘላለም ሲቀመጡ እንደ ዘለቀ በየነ ዓይነት ከሃዲ ፋሽሽቶች ደግሞ ለዘላለም በጭንቀት በሽታ ሲሰቃዩ ይከርማሉ ። በታሪክም ውስጥም የተዋረደ ቦታ ይዘው ይኖራሉ ።

ሰለኛ የሚያስብ ሁሉ በሰላም ይክረም !!!

ይህንን ፅሁፍ በሚመለከት አስተያየት መስጠት ለምትፈልጉ በዚህ ኢሜል አድራሻ ተጠቀሙ።

beljig.ali@gmail.com